# የተሐድሶ አብያተክርስቲያናት አለምአቀፍ ሕብረት

## ሥላሴን ማምለክ
## (እ.ኤ.አ) ሰኔ 2010 የተሻሻለ

## በምዕተ ዓመታትና በመላው አህጉራት የክርስትናን ጥበብ መቀበል፣ ማካፈል እና ከትውልድ ወደ ትውልድ ማሸጋገር የ2010 ዕትም

### መግቢያ፡-

በብዙ ባህሎች ዘንድ ጥበብን መካፈል የተለመደ ነገር ነው፤በምስራቅና በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ በተለይም ለመማርና ለማካፈል ምቹ የሆኑ ባህሎች ባጠቃላይ በትውልዶችና በምዕተ አመታት በሁለቱ ማለትም በቃልና በጽሁፍ ጥበብን ማካፈል በተለያዩ አገሮችና ትውልዶች ዘንድ የተለመደ ነገር ነው፡፡ጥበብን መካፈል በቅዱስ መጻሕፍት ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡መጽሐፈ ምሳሌን፣ መዝሙረ ዳዊትን፣የኢየሱስ የተራረው ስብከትን እና አብዛኛው የጳውሎስ ማበረታቻ መልዕክቶችንም ሁሉ ያካትታል፡፡ጥበብን ማካፈል ማለት ከክርስቶስ አካል ከሆነችው ከቤተክርስቲያን ጋርም መተሳሰር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጥበብን ማካፈል ለአለማቀፍ የክርስቲያን ሕብረት ማዕከላዊ ልምምድ ነው፡፡ ልክ እንደዚህ የተሀድሶ አብያተክርሰቲያናት አለማቀፍ ሕብረት (WCRC) የምንካፈለው ጥበብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥበብ ታማኝና ትክክለኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥበብን ማስተጋባት ማለት ነው፡፡ ይህም የታማኝ የቃሉ ምስክር ወይም “የእግዚአብሔር ጥበብ” (1 ቆሮ1፡24) ማለት ነው፡፡ስለዚህ ይህ ጥበብን ማካፈል የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ የሆነውን “የጥበብ መንፈስ” (ኤፌ1፡17) ነው፡፡ እንደ ባቢሎን ሳይሆን እንደ ጴነጠቆስጤ ቀን በመሆን ምልክት መሆን ነው፡፡

የክርስቲያን አምልኮ ልምምድ በተመለከተ የዚህ የምሳሌዎች ስብስብ ዓላማ የክርስቶስ አካልን በታማኝነት ለማገልገልና ለአገልግሎት እንዲጠቅም ማድረግ ነው፡፡ይህ የምሳሌዎች ስብስብ የተሰበሰበው በተሀድሶ ክርስቲያኖች አማካኝነት ነው፡፡ስብስቡ በአንድ ጊዜ ሁሉንም ያካተተ፣ የጋራ ተሳትፎን የሚያንፀባርቅ፣ ቅዱስ፣ ሁሉ አቀፍና ሐዋሪያዊት ቤተክርስቲያን ይዘት ያለው ሲሆን እንደዚሁም ልዩ ስብስብ፣የተለየ ታሪክ የሚያንፀባርቅ፣የስነመለኮት ተአሚኒነት ያለው፤እና በአለማቀፍ የተሀድሶ ማህበረሰብ የሚዘወተርም ነው፡፡ይህ ሰነድ የተፃፈው ለሁለቱም ማለትም የተሀድሶ አብያተክርስቲያናት አለማቀፍ ትብብር (WARC) በጋና አክራ 2004 በነበረው ስብሰባ እና በኔዘርላንድ ኡትረኽት በ2005 የተሀድሶ አብያተ ክርስቲያናት የምክክር ጉባኤ ( REC) ለነበረው ተልዕኮ ምላሽ እንዲሆን ታቅዶ ነው፡፡ይህንንም የሁለቱ ድርጅቶች አባል አብያተክርስቲያናት የተወሰነ ጊዜ ግኑኝነት

በመቀጠል በአምልኮ ዕቅድ አወጪዎች ዳብሮ ከተዘጋጀ በኋላ ለ2010 WCRC ለተባበረው ጠቅላላ የምክክር ጉባኤ በአሜሪካን ሀገር በሚሽጋን ግዛት በግራንድ ራፒድስ በፓስተሮች፣ በአስተማሪዎች፣ እና በአለማቀፍ ደረጃ በሌሎችም ሚዎች በተሀድሶ ባህል ወስጥ ያሉትም ይሁኑ ከተሀድሶ ባህል ውጭ ያሉትን ሁሉ ባሳተፈ ሚልኩ ወይይት ተደርጎበት ዳብሮአል፡፡በሚጨረሻም በተባበረው ጠቅላላ ጉባኤ በአምልኮና በመንፈሳዊ ተሀድሶ ዘርፍ ፀድቆ ተዘጋጅቶአል፡፡

ይህ ሰነድ የተዘጋጀው ለአምልኮና ለመንፈሳዊ ተሀድሶ ራዕይ እንዲሰጥ ታስቦና በእርሱም እያንዳንዳችን ወደ ጠለቀና አስፈላጊ ወደሆነ ራስን ወደ መግለጥ እንዲጋብዘን ታስቦ ነው፡፡ ይህ ሰነድ በአባል ቤተክርስቲያናት ላይ የልምምድ ጥርቅም ጫና እንዲፈጥር ተብሎ የተቀረፀ አይደለም፡፡ ወይም ደግሞ በአባል ቤተክርስቲያናት አምልኮ የዚህ ጥበብ ሙላት እንዲገልጥ ታቅዶም አይደለም፡፡ ነገር ግን ሰነዱ የተዘገጀው ለብዙ ጠቀሜታ ሲሆን ከእነዚህም ወስጥ፡ -

1. ይህ ሰነድ በአንድ በተወሰነ ማህበረምዕመን ጥቅም ላይ ሊወል ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ በአጥቢያ ደረጃ ለሚደረጉ ልምምዶች በተለይም ሰለስጦታዎች ተግዳሮቶች፣ስለጠንካራ እና ደካማ ጎን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በቤተዕምነት ደረጃ ለሚደረግ ወይይት ጥቅም ላይ ሊወል ይችላል፡፡

ወይይቱን የሚምሩት ከእያንዳንዱ ምሳሌ በኋላ ቆም በማለት እንዲህ ሊጠይቁ ይችላሉ "እንዴት ነው ይህንን ጥበብ ለማለማመድ እግዚአብሔር ስጦታ የሰጠን?" "በምንስ መንገዶች ነው ይህንን ጥበብ በበለጠ በታማኝነት በሥራ ላይ እንድናወለው እግዚአብሔር የሚጠራን?" እንደዚሁም "በሌላ በምን ሚልኩ ነው የዚህ የጥበብ ልምምዳችን ከዚህ ዋና ሀሳብ ጋር አያይዘን የምንገልጠው?" እያንዳንዱ ምሳሌ የተቀረፀው ለወይይታችንን ሚልስ በሚሰጥ ሚልኩ ሲሆን በተለይም በስነመለኮት ሚረዳታችንና በልምምዳችን መካከል ያለወን ግንኙነት እንዲቃኝ ተደርጎ ነው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ በምስክርነት ላይ ያተኮሩ ወይይቶችን እና መንፈሳዊ ነገሮችን መለየት በማንኛወም ፍሬያማ አገልግሎት አወድ ሁነኛ ነገሮች መሆናቸወን ያስገነዝባል፡፡

2. ይህ ሰነድ በማህበረ ምዕመን ወስጥ እና በማህበረ ምዕመናን መካከል የሚደረግ ወይይት ሊቀርጽ ይችላል፡፡ በተለይም ጭራሽ በተለያየ ባሕልና አወድ የምዕመናንና የቤተዕምነቶችን ወይይት ቅርጽ ሊያሲዝ ይችላል፡፡

ወይይቱን በመቅረጽ ሂደት ላይ ያሉቱ ከእያንዳንዱ ምሳሌ በኋላ ቆም በማለት እንዲህ ሊጠይቁ ይችላሉ፡- "እንዴት ነው እግዚአብሔር ከነ ልዩ ልዩ ባህላችንና ልምምዳችን ይህንን

ጥበብ እንድንለማምድ ስጦታ የሚሰጠን?" እና "ደግሞስ በምን መንገድ ነው እግዚአብሔር ይህንን በበለጠ በታማኝነት በሥራ ላይ እንድናውለው የሚጠራን በተለይም እርስበርሳችን ልንለማምርበት ከምንችልበት ብርሃን አኳያ ሲታይ ምን ዓይነት ይዘት አለው?"

## 3. ይህ ሰነድ ለበለጠ መሻሻልና በጥልቀት ለጥናት ለመተባበር የሚጋብዘን ሰነድ ነው፡፡

እያንዳንዱ ምሳሌ የምርምር ማጠቃለያ ውጤትና ክርስቲያናዊ ሐሳብ ሲሆን የተገነባውም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥልቅ ትንተና፣በስነመለኮት ሐሳብና በታሪክ ሊቃውንት ጭምር ነው፡፡እያንዳንዱ ምሳሌ ቀጣይነት ባለው በእውነተኛ በደቀመዝመሮነት ብርሃን ዕይታ በተጨማሪ በታማኝት ሊጨመቅ ይችላል፡፡ይሁን እንጂ ይህ ስብስብ የመጨረሻ ወይም የተሟላ ተደርጎ የተቀረፀ አይደለም፡፡ ሰነዱ የተቀረጸው በእርግጥ ክፍት ተደርጎ ነው፡፡ምክንያቱም ማንኛውም አባል ቤተ ክርስቲያን ወይም ሕብረት የመሰረቱ አጋሮችም ይሁኑ በቀላሉ ራሳቸው ካዘጋጁት ጋር ሊጨምሩት ይችላሉና፡፡ የአለም የተሀድሶ አብያተ ክርስቲያናት (WCRC) ጉባኤም ቢሆን ወደፊቱ ሊያስተካክለው በሚችል መልኩ የተዘጋጀ ሰነድ ነው፡፡እንዲሁም ሰነዱ ሌሎች ወደፊት ሊነሱ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ሊቀርፉ የሚችሉ ምሳሌዎችንም ማከል እንዲቻል ታስቦ ነው የተዘጋጀው፡፡

ይሁን እንጂ የዚህ ሁሉ ጥቅም የመጨረሻ ግብ ወይይት ለማሳደግ ወይም የተሻለ ውጤታማ ሰነድ እንዲሆን ታስቦም አይደለም፡፡ነገር ግን የመጨረሻ ግብ እንዲሆን የታሰበው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት የታመነ በምስጋና የተሞላ የስላሴ አምልኮ በመሳል ምሳሌ ለመስጠት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እንድትጠነክር እግዚአብሔር አምላክ እነዚህ ቃሎች እና እነዚህንም ቃሎች ለመጽናት የሚጥሩ ሁሉ ይባርክ፡፡

<u>ማስታወሻ</u>፡ በዚህ ሰነድ ዕትም ወስጥ "ቤተክርስቲያን" "ማህበረ ምዕመን" እና "ማህበረሰብ" የሚሉት ቃላቶች እንደአስፈላጊነቱ ተራ በተራ አባል ቤተክርስቲያናትን በማገልጥ መልኩ በሥራ ላይ ወለዋል፡፡ እንደዚሁም "ብሩክ" እና "አስተዋይ" የሚሉ ቃላቶች በዚህ ሰነድ ወስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ ወለዋል፡፡ በተለይም "ብሩክ" የሚለው ቃል በመሰረታዊነት እኛ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስንጠብቅ ከእግዚአብሔር ከአምላካችን የሚመጡ በረከቶችን ለመረዳት በሚያስችለን መልኩ ጥቅም ላይ ወሎኣል፡፡እንደዚሁም "አስተዋይ" የሚለው ቃል ማህበረ ምዕመናን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማየት የሚወስኑት ወሳኔ በማገልጥ መልኩ ተካትቶል፡፡ከአባል አብያተክርስቲናት በሚሰጠን ምላሽ መሰረት ይህን ሰነድ በበለጠ ለማሻሻል በጉጉት እንጠብቃለን፡፡

## ፩. የተጠራና ይቅር የተባለ ሕዝብ በኢየሱስ ስም ይሰበሰባል

### 1.1 በሥላሴ ተጠርተናል

በሥላሴ እንደተጠራ በጥልቀት የሚያውቅ እና ሥላሴንም ማዕከል በሚያረግ የሚያመልክ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተባረከ ነው፡፡

እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በቃሉና በመንፈሱ ሕዝቡን የሚሰበስብ፣ የሚጠብቅ እና ለቤተክርስቲያን የሚጠነቀቅ[1] ነው፡፡

ልዑልና ክቡር የሆነው እግዚአብሔር አምላካችን "የማይታይ አምላክ ምሳሌ"በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ተገልጦአል፡፡

በሥላሴነቱ አምልኮዋችንን የሚቀበል አምላክ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን አምልኮዋችን ወጤታማ እንዲሆን የሚያደርግ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከፍ የሚያደርገን፣ ማሳዋዕታችንን ፍፅም ካህን በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የሚቀድስ፣ በምድር ላይ በነበረው ሕይወት "ለአብ" እዉነተኛ ምስጋናን በሰዋ በመንፈስ ቅዱስ ፍፁም ደስተኛ በሆነ (ሉቃ10፡ 21) እና አሁንም "ስለእኛ ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት በሚኖርው በኢየሱስ "(ዕብ7፡ 25) መሆኑን በማንዘብ በታላቅ ምስጋና እዉቅና የሚሰጥ ማህበር ብሩክ ነው፡፡

[1] የቤላሀር የዕምነት መግለጫ እና የሂደልበርግ ካታኪዝም

እግዚአብሔር እንዲባርካቸው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደ ባርካቸው በሚረዳት እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ አማኞችን የሚያነሳሳ ማሕበረ ምዕመን ብሩክ ነው፡፡

ሥላሴ የሆነውን እግዚአብሔር አምላክ እርሱም የሚወቅስ ፣ የሚያርም የሚያስተምርና የሚመግብ አምላክ መሆኑን በሚረዳት እርሱንም ደግሞ በማምለክ እንደተባረከ በእርግጥ የተረዳ ማህበረምዕመን የተባረከ ነው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ አማኞችን ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር የሚያስተሳስር፤ ቃሉን በማወጅ የሚቀደስ ተግባር ያለውና በሕብረት ፀሎት፣በውሃ ጥምቀትና በጌታ እራት እንደዚሁም በምስክርነት፣ በስጦታ እና ሕብረት በማድረግ በአማኞች መካካል አንድነት የሚያፀና ማህበረ ምዕመን ብሩክ ነው፡፡

**1.2 በሕብረት ጉባኤ፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ በሞላ** ማሰብሰቡን የሚይተው (ዕብ10፡25) የአምልኮ ማህበረሰብ አስተዋይ ነው፡፡ ነገር ግን በኢየሱስ ስም በፍቅር የሚሰበ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለማወጅ የሚዜጋ ምስጋናና ፀሎት የሚሰዋ እና የቤተክርስቲያን ሥርዓቶችን የሚያከናውን ሊሆን ይገባል፡፡እነዚህ እያንዳንዱ ተግባራት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ተግባር ነው፡፡ “የንጉሥ ካህናት” (1ጴጥ2፡9)

ሁሉንም አምላኪዎች በተለይም በባህል ምክንያት በተለየ ሁኔታ የሚገደቡትን “አካል ጉዳተኞች”ወደ ሙሉ አምልኮ በማጋበዝ በተረዳና በነቃ ተሳትፎ በሕብረት አምልኮ እንዲካፈሉ በማድረግ፤ለእግዚአብሔር አምላክ በተሰጠ ሙሉ ልብን ፣ነፍስንና አዕምሮን በማሳተፍ ስለራሳቸው አምልኮ በጥልቀት እንዲረዱም በማድረግ በስፋት ለአምላክ በሚቀርበው በምስጋና ዝማሬ የሚያሳትፋቸው ማህበረ ምዕመን ብሩክ ነው፡፡

በአምልኮዋቸው ላይ የክርስቶስ አካል አንድነትን የሚገልጡ፥ የመንፈስን አንድነት በሰላም ማሰሪያ የሚያፀኑ፣ በእግዚአብሔር ስጦታና በመጥራቱ

አንድነት ሽማግሌወችና ወጣቱን የሚቀራርቡ እና በሁሉም ቦታና ጊዜ አማኝነታቸውን በመግለጥ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የጋራ ጥሪወን[2] የሚከፈል ማሕበረ ምዕመን ብሩክ ነው፡፡

## 1.3 መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ በስሜቱም በምክንያት ሰጪነትም እንደሚሰራ የሚያስተውል፣ በአስገራሚ ሁኔታም ይሁን በመንፈሳዊ ልምምድ ወቅትም እንደዚሁም በጽኑ ፀሎት በታቀደ ሜሉኩም ይሁን በአገልግሎት እና ቅጽበታዊ በሆነ ድንገተኛ መገለጦችም ቢሆን እንደሚሰራ የሚረዳ የአምልኮ ማሕበረሰብ አስተዋይ ነው፡፡

የአምልኮ የሚጨረሻ ዋጋ ወይም መንፈሳዊ ኃይል በሰው ችሎታ ላይ ያልተመሠረተ፤ በሰው አስተሳሰብ፣ በአዕምሮ ችሎታ ወይም በስሜቶች የሚለካ ሳይሆን ነገር ግን ከእነዚህ የትኛወንም ለማጠቀም ማምረጥ በሚችል ወይም ሁሉንም ማጠቀም ደግሞ በሚችል ከመንፈስ ቅዱስ የሚመጣ መሆኑን የተረዳ፤ በእርግጥም አምልኮ ልንቀበለው የሚገባ ስጦታ እንጂ ልንፈጽመው የተገባ ተግባር አለመሆኑን የተገነዘበ የአምልኮ ማህበረሰብ አስተዋይ ነው፡፡

## 1.4 ባህልን ማገረታታት እና መቃወም

ወደ እያንዳንዱ ባህል በመጣው ነገር ግን በየትኛወም ባህል ባልተጠለለፈዉ የኢየሱስ ወንጌልሜልካም ዜና ለማዝበር በንቃት በመንቀሳቀስና ባለማቋቋሙ የወንጌልን እውነት የሚዳደር ማንኛውንም የባህል ተፅዕኖ በመጣስ በዓለም "ወስጥ" ነገር ግን "ከዓለም" መሆን የማትፈልግ ቤተክርስቲያን (ዮሐ 15፡19) አስተዋይ ናት፡፡

የኢየሱስን ወንጌል በብዙ ባህሎች ወስጥ እንዲገባ የምትጥር፣ ባህልንም ተሻጋሪና አወዱን የጠበቀ እንዲሆን የምታደርግ እንደዚሁም ደግሞ የወንጌልን እውነት የሚቃወምን ባህል[3] ጥሳ የምትሄድ

[2] በግራንድ ራፒድስ ለነበረው ጉባኤ ከWCRC ሰነዶች የተወሰደ

[3] አምላኮና ባህል ከሚለው ከሉተራን አለማቀፍ ፌደሬሽን ኬንያ ሰነድ የተወሰደ

ቤተክርስቲያን ግሩም ከመሆንዋ በተጨማሪ አስተዋይ ናት፡፡

## 1.5 የተዋጀው ፍጥረት መልካምነት

በፍጥረት ሁሉ በቀረበው መሠረት አምልኮን ግልጽ በሆነ የምስጋና ዝማሬ የሚያጅብ ማህበረ ምዕመን አስተዋይ ነው፡፡

ፀሎትንና የምስጋና ዝማሬን በማጉላት በታላቅ ፈገግታና ደስታ በተጨማሪም በቃሉ፣ በጥምቀተ ውሃ፣ በሕብስቱና በወይኑም እንደዚሁም እግአብሔር ለሕዝቡ ጥቅም ባዘጋጀው የፀጋ ስጦታዎች አምልኮ ሕይወት ሰጪ እውነታ መሆኑን ተረድቶ የሚደሰትበት ማህበረ ምዕመን አስተዋይ ነው፡፡

## 1.6 የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማምራት

አባላቶቹን ለአገልግሎት የሚጠራ፣ የሚያሰለጥን፣ የሚያፀና እንደዚሁም የሚሄነት ፀጋ ያላቸውን ከሁሉም ፆታ፣ ከሁሉም ዕድሜ ክልል፣ ከሁሉም ጎሳ ወይም ዘር ፀጋቸውን በማየት በሥነ መለኮትና በአምልኮ ልምምድ መሠረታዊ ትምህርት በመስጠት በማማከር የሚያሰማራ ማህበር አስተዋይ ነው፡፡

ሁሉንም የማህበሩን አባላት የሚያስታጥቁ፣ እንደዚሁም ወደ ሙሉነት የሚያደርሱና ባለአዕምሮና ንቁ ተሳታፊዎች[4] በማድረግ የክርስቶስ አካል ለሆነችው ቤተክርስቲያን አካል ያልሆኑትን ሁሉ ርሕራሄን ለማሳየት እንዲጠነቀቁ በመቅረጽ አምላኮን የሚመሩ መሪዎች አስተዋዮች ናቸው፡፡

## 1.7ሥዕላዊ መግለጫ

ስብከተ ቃሉን፣ ፀሎቶችንና ዝማሬዎችን በቃላት ብቻ ሳይሆን በልዩ ሁኔታ በስዕላዊ መግለጫ ማለትም እያንዳንዱ የማህበሩ አባል እግዚአብሔር በሰጠው ፀጋ በተለይም በሚዚቃ፣ በሽብሸባ፣ እንዲሁም በንግግርም በዝምታም ቢሆን፣ በሚታዩ ሥዕሎች፣ ዲዛይኖች በማሳሰሉት ሁሉ የሚያወጅ ማህበረ ምዕመን ብሩክ ነው፡፡

ስጦታቸውን የእግዚአብሔርን መልካምነት እንዲመሰክር፣ ለእግዚአብሔርም ምስጋና እንዲያመጡ ለንሰሀ የሚጋብዝ በማድረግ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያስገዙ ችሎታ ያላቸው ሁሉ የተባረኩ ናቸው፡፡

---

[4] ሲኤፍ- ቫቲካን ፪

በሁለተኛይቱ ትዕዛዝ
የተከለከለውንና እንደዚሁም
ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል
የተደገፈውን ባለማሳት እንደ
እግዚአብሔር ቃል በእግዚአብሔር
ሕዝብ ለአገልገሎት የሚያጠቁ
ሰዓሊን የተማሰገኑና አስተዋዮች
ናቸው፡፡

ካለፉት ዘመናትና ከሌሎች
ባህሎች የተወሰዱ የታመኑ
የዝማሬና የአምልኮ ሥራዎች ችላ
ባለማከት የምትጠቀም፣
በቤተክርስቲያን
በአለማቀፋዊነት የምትደሰት፣
እንደዚሁም ደግሞ በአምልኮና
በአዲስ ዝማሬንና በአምልኮ
ሥራዎች የተሞላ ችሎታን
የምታበረታታ ቤተክርስቲያን
አስተዋይ ናት፡፡

## ፪. የእግዚአብሔርን ቃል በደስታ ማወጅ

### 2.1 መንፈሱና ቃሉ

መንፈስ ቅዱስ
የእግዚአብሔርን ሕዝብ
ልቦናንና አይምሮ እንዲከፍት
በታላቅ አክብሮት ሚልስ
ባለው ፀሎት ታጅቦ
የእግዚአብሔርን ቃል
በዕምነት እንዲሰበክ
የሚያደርግ ማህበረ ምዕመን
የተባረከ ነው፡፡

### 2.2 ክርስቶስን ያማከለ ቃል ስፋት

በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ
ኪዳን እንደተገለጠው
በንባብና በስብከት
የእግዚአብሔርን ቃል
ስፋትንና ጥልቀት በሚገልጥ
ሚልኩ አማኞችን በመመገብ
ሁልጊዜ የክርስቶስ
ኢየሱስን ወንጌል መላት
የሚወጅ ማሕበረ ምዕመን
አስተዋ ነው፡፡

### 2.3 ለእረፍትና ለምስክርነት፣ ለሰላምና ለፍትህ መጥራት

የእግዚአብሔርን ቃል
ለሚያለቅሱት መጽናናትን
የሚሰጥና የእግዚአብሔርን
አገዛዝ የሚቃወሙትን ደግሞ
የሚገሥጽ በሚድረግ የሚወጅ
ማህበረ ምዕመን ብሩክ
ነው፡፡

አድማጮቹን ክቡር የሆነውን
የእግዚአብሔርን ፀጋ
እንዲቀበሉ የሚጋብዝ
እነደዚሁም ከክፋትና
ከሃጢአት ወደ ክርስቶስ
እንዲመለሱ የሚሰብክ፤
ሰላምንም የሚያወጅ “ፍርድን

የራሱንም ፀሎት ቅርፅ የሚሰጥ አድርጎ በማንዘብ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለፁት የምስጋናና የውዳሴ ፀሎቶች የሚሮርና እርሱንም የሚከል (ለምሳሌ መዝ 136) ማህበረ ምዕመን አስተዋይ ነው፡፡

## 3.2 በመንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ስም መፀለይ

ባረገውና ደግሞም ሁልጊዜ ከእኛ ጋር በሚሆነው ጌታ እውቅና በመስጠት ከእርሱ ጋር ያለንን ሕብረት በማጠንከር በኢየሱስ ስም የምትፀልይ ቤተክርስቲያን ብሩክ ናት፡፡

በመንፈስ ቅዱስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚፀልይ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ የሚፈልግ፣ በምንፀልይበትም ጊዜ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ድካማችንን እንደሚያግዝ የሚያውቅ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለእኛ እንደሚማልድ (ሮሜ 8፡26-27)፣ እንደዚሁም መጋደላችን "ከጨለማ ዓለም ገዥች ጋር በሰማያዊም ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር" (ኤፌ 6፡12) መሆኑን የተረዳ የአምልኮ ማህበር ብሩክ ነው፡፡

## 3.3 የሰው ልምምድ ልክ

እውነተኛና የታመነ ፀሎት ወደ እግዚአብሔር እንዲደረግ የምታበረታታ፣ የሰውን ልምምድ ልክ በሚገልጥና "ለነፍስ ክፍሎች" ደግሞ በሚደርስ ሁኔታ፣በመናገር በመዘመር ወይም በፀጥታም ቢሆን፣በሽብሸባ በድራማ ወይም በሥዕላዊ መግለጫ በፀሎት በደስታና በለቅሶ፣በመታመንና ተስፋ በመቁረጥ፣በመቃተትና በምላጃ፣ በዕምነትና በምስጋና፣በፈውስና በተስፋ የመዝሙረ ዳዊትን ምሳሌነት የምትከተል ቤተክርስቲያን አስተዋይ ናት፡፡
ለራስዋ ምቾት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን እግዚአብሔር ለሚወደው ዓለም ሁሉ ምቾት[5] የምትፀልይ ቤተክርስቲያን ብሩክ ናት፡፡

## 3.4 ስጦታና መባ

[5] ይህ አረፍተ ነገር "የነፍስ ክፍል" ከሚለው ከጆን ካልቪን የመዝሙረዳዊት ማብራሪያ የተወሰደ ነው፡፡

ከታላቅ ምስጋና ጋር ስጦታን ማስጠት፣ገዘብን፣ጊዜንና ልዩ ችሎታን የአምላኮ አካል በሚድረግ ማስዋዕት አድርጋ የምታቀርብ ቤተክርስቲያን አስተዋይ ናት፡፡

ዘመንዋን በሙሉ እግዚአብሔርና ጎረቤትዋን ለማገልገል የምታውል እና አማኞችን ደግሞ የእግዚአብሔር ስጦታ በሆነው ላይ ሚልካም ማጋቢያች እንዲሆኑ እንደ ተጠሩ የምታስረግጥ ቤተክርስቲያን አስተዋይ ናት፡፡

**፬. ማጥመቅና በደስታ መመገብ**

**4.1 ስለማጥመቅና የጌታንም ዕራት ስለመውሰድ የኢየሱስ ትዕዛዝ**

"ደቀመዛሙር በሚድርግ" ደግሞም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በማጥመቅ እንዲታዘዙ የምታስተምር (ማቴ 28፡20) ደግሞም "ለመታሰቢያዬ እንዲሆን ተመገቡ" (ሉቃ 22፡19-20) በማለት ኢየሱስ ያዘዘውን ሁሉ እንዲፈጽሙ የምታበረታታ፣ እነዚህ ምልክቶች መቀበል ደግሞ እግዚአብሔር እኛን ለመመገብ፣ ለሚጽናናትና ለሚጽናትም እንደዚሁም ደግሞ እንድንፈተን፣ እንድንሚር እና እንድንለወጥ መሆኑን በሚረዳት የኢየሱስን ትዕዛዝ በታማኝነት የምትተገብር ቤተክርስቲያን ብሩክ ናት፡፡

**4.2 ጥምቀት**

የአማኞች እውነተኛ ማንነት የሚገለጠው በክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑን የሚያወጅ ማህበረ ምዕመን ብሩክ ነው፡፡

የወሃ ጥምቀት የእግዚአብሔርን ተስፋ ማህተምና ምልክት መሆኑንና ደግሞም የሚያነጻን፣ወደ ክርስቶስ አካል የሚጨምረን፣ እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ እንዲያስታጥቀን እና በክርስቶስ ኢየሱስ የሚገኘውን ለአዲስ ሕይወት ትንሣኤ ምልክትና የቃል ኪዳን ማህተም መሆኑን የሚያወጅ ማሕበረ ምዕመን ብሩክ ነው፡፡

የውሃ ጥምቀት
የእግዚአብሔርን ጥሪ
ማህተምና ምልክት የሆነበት
ምክንያትም ከክፋትና
ከሃጢያት ርቀን ክርስቶስን
በመከተል በእርሱም ደግሞ
ያገኘነውን አዲስ ሕይወት
ለማጽናት በተለወጠና
በተቀደሰ ሕይወት ለመኖር
መሆኑን የሚያውጅ ማህበረ
ምዕመን ብሩክ ነው፡፡

የውሃ ጥምቀት በክርስቶስ
ያገኘነውን አዲስ ሕይወት
በማንፀባረቅ በታደሰ ሕይወት
በቅድስና የገባነውን
ቃልኪዳን በማጠበቅ
በታማኝነት እንድንኖር
የሚረዳን ምልክትና
የቃልኪዳን ማህተም መሆኑን
ተረድቶ በደስታ ሥርዓቱን
የሚፈጽም ማህበር አስተዋይ
ነው፡፡

## 4.3 የጌታ ዕራት

እንደ ምስጋና በዓል
በመቁጠር ደግሞም ሕብረት
ለማድረግ እና ተስፋን
ለማስነቅ የጌታን ዕራት
ሥርዓት ዘወትር በደስታ
የምታከናውን ቤተክርስቲያን
ብሩክ ናት፡፡

እግዚአብሔር በክርስቶስ
ኢየሱስ የፈጠረውንና
የዋጀውን ታላቅ ነገር እና
ሕብስቱን በመቁረስ ጊዜ
የሚገኘውን የመገኘቱ ሕልውና
የሚያስብ ብቻ ሳይሆን ነገር
ግን ከክርቶስ ኢሱስና
ከአካሉ ጋር አንድ መሆኑን
በክብር የሚቀበልና ደግሞም
ወደፊት የሚሆነውን
የመንግስቱን ግብዣ በአንክሮ
የሚጥባከት ማህበር ምዕመን
ብሩክ ነው፡፡

ብዙ ብልቶች ነገር ግን
አንድ አካል መሆናችንን
በማወቅ፣ በእውነትና በፍቅር
አንዱ ለሌላው ርሕራሄን
በመግለጥ (1ቆሮ 11፡29-33) በዓለም ላይ
የምናገለግለውን የርሕራሄ
አግልገሎት እንዲደገፍ
የእግዚአብሔርን ርሕራሄ
ለእኛ በሚያንፀባርቅ መልኩ
ይህንን ዕራት "የጌታ ሥጋ
መሆኑን" በሚረዳት የሚከፈል
መህበር ምዕመን ብሩክ
ነው፡፡

## ፭. በኢየሱስ ስም የሚያገለግል የተባረከና የተላከ ሕዝብ

## 5.1 በእግዚአብሄር መላክ

የኢየሱስን የምስራቹን ወንጌል ለማወጅና ደግሞ በኢየሱስ ስም በዚህ ዓለም ላይ የፈወስ ምልክት ሆኖ በመኖር ለእግዚአብሔር ቸርነት ጥሪ ደግሞ ምላሽ ለመስጠት የሚተጋ ማህበረ ምዕመን ብሩክ ነው፡ ፡

## 5.2 በየዕለቱ ማምለክ

የእግዛብሔርን ቃል በማንበብና በማሰላሰል ላይ ትኩረት በማድረግ በየዕለቱ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት በመፈለግ፣ የምስጋና ፀሎትንና ምልጃ በማቅረብ፣ መዝሙር በመዘመር፣ በውዳሴ እና በመንፈሳዊ ዝማሬዎች በመቃኘት ደግሞም እግዚአብሔርን “ርጭ ባለ ፀጥታ” በማዳመጥና (1ነገ 19፡ 12) ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ፊት በመኖር ሁሉንም አማኞች እንዲያመልኩ የሚያበረታታ የአማኙንም ዕምነት የሚገነባ ማህበር አስተዋይ ነው፡ ፡

## 5.3 ወንጌል ሥርጭትና ርሕራሄ

በግል ህይወትና በማህበር አምልኮ የርሕራሄ አገልግሎት በመስጠት እንግዶችን የሚቀበሉና የሚያስተናግዱ፣ ድሆችን፣ የተገለሉትን፣ የታመሙትንና፣ የተረሱትን በማስታወስ ከእግዚአብሔር ክንፍ ጥላ ሥር ማጠጊያ እንዲያገኙ የሚያደርጉ ማህበራት ብሩካን ናቸው፡ ፡

የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እንዲሆኑ ሁሉንም ሕዝብ የሚጋብዙ፣ አንፅኦት በመስጠት እንዲጠምቁና በእምነታቸውም እንዲያድጉ እንዲተከሉ የሚያደርጉ ማሕበራት ብሩካን ናቸው፡ ፡

## 5.4 በአምልኮ ማደግ

“በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋና እወቀት እንዲያድጉ” (2ጴጥ3፡ 18) በሁሉም የዕድሜ ክልል ያሉትንና ምንም ዓይነት ችሎታ ያላቸውን አማኞች የሚጋብዙና የሚያበረታቱ ማህበረ ምዕመናን ብሩካን ናቸው፡ ፡

በቃሉ፣ በአስተምህሮት፣ በልምድና በመንፈስ ፍሬ ታማኝ የሆነውን መልካም ግኑኝነት የሚንከባከቡ ማህበረ ምዕመናን ብሩካን ናቸው፡ ፡

አምላኮ ጥልቀት ያለው እንዲሆን የሚጋገሩና

የአምልኮ ልምምድ ምን
ሊመስል እንደሚገባው
የሚያስተምሩ ማህበረ
ምዕመናን አስተዋዮች
ናቸው፡፡

## 5.5 አምልኮ፣ መሥራትና ቅን ፍርድ (ፍትህ)

የማህበር አምልኮዋቸው ወደ
ኢየሱስ ክርስቶስና ኢየሱስ
ስለ እግዚአብሔር መንግሥት
ወደ ተናገረው መልዕክት
የሚጠቁም ማህበረ ምዕመናን
ብሩካን ናቸው፡፡

በዓለም ያላቸው ምስክርነትና
የሕብረት አምልኮዋቸው
የሚጋጭ ወጥ የሆነ እና
ለእግዚአብሔር ቃል የታመኑ
እንዲሁም አምልኮዋቸውንና
ምስክርነታቸው የመንፈስ
ቅዱስ ሥራ መሆኑን የሚያሳዩ
ማህበረ ምዕመናን ብሩካን
ናቸው፡፡